# በወንጀል ተግባር የተገኘ  ገንዘብን ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ አዋጅ

# አጭር ማብራሪያ

## መግቢያ

ኢትዮጵያ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን እንዲሁም የጅምላ ጨራሽ መሳሪያዎችን ብዜት በገንዘብ የመርዳት ወንጀል የኢኮኖሚ ደህንነት ሥጋት ብቻ ሳይሆን የአጠቃላይ የፋይናንስ ሥርዓቱ የተረጋጋ፣ ግልፅኝነት ያለውና ጤናማ እንዳይሆን በማድረግ አጠቃላይ የፋይናንስ ሥርዓቱን የሚያናጋ ወንጀል ነው፡፡ በሌላ በኩል  ተፅዕኖውም ድንበር ተሻጋሪና ዓለም አቀፋዊ ችግር በመሆኑ ወንጀሉን ለመዋጋትም በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የሚደረገውን ጥረት አካል ለመሆን ኢትዮጵያ ወንጀሉን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ራሱን የቻለ የህግ ማዕቀፍ በማውጣት ተግባራዊ እያደረገች ትገኛለች፡፡

በመሆኑም በተግባር ላይ ያለው ህግ መሠረታዊ  ዓላማዎች ለማጠናከር በተለይም በወንጀል ተግባር የተገኘ ገንዘብን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ  ወንጀል የሀገሪቱ የደህንነት ስጋት ብቻም ሳይሆን የፋይናንስ ሥርዓቱ የተረጋጋ፣ ግልጽነት ያለው ጤናማና ቀልጣፋ እንዳይሆን ስለሚያደርግ ይህንን ለመዋጋት የሚደረገውን ጥረት ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን ለማስቻል አስፈላጊ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ድርጊቱን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥረት እየተደረገ መሆኑ እና ኢትዮጵያም የዚህ ዓለም አቀፍ ጥረት አካል መሆኗ እንዲሁም ወንጀሉ የሚያስከትለው አሉታዊ ተፅዕኖው ድንበር ተሻጋሪ ስለሆነ የመዋጋት ስልቱም የጋራ ጥረት የሚያስፈልግ በመሆኑ ሀገራት ግዴታ ስለተጣለባቸው ይህንን ግዴታ ይበልጥ አጠናክሮ እንዲሄድ ለማስቻል፡፡

የፋይናንስ ደህንነት ማዕከሉ ዘርፉን የሚመለከቱ አዳዲስ የህግ ማዕቀፎችን በማውጣት እና በተግባር ላይ ያሉ የህግ ድንጋጌዎችን ዘርፉን በተመለከተ ከፋይናንስ ግብረ ኃይሉ ምክረ ሃሳብ ለሎች ኢትዮጵያ ፈርማ ከተቀበለቻቸው ስምምነቶች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ ወቅቱን ጠብቀው እንዲሻሻሉ በማድረግ በተግባር ያጋጠሙ ክፍተቶችን በማሟላት መሥራት አስፈላጊ መሆኑ ታሳቢ በማድረግ የህግ ማዕቀፉን ማሻሻል አስፈላጊ እንዲሆን አድርጎታል፡

## የአዋጁ አስፈላጊነት

በወንጀል ተግባር የተገኘ ገንዘብን ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ሰፊ ስራዎችን ውጤታማ በሆነ መንገድ መስራት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በፊት በስራ ላይ የነበረው አዋጅ ወንጀሎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ በርካታ ጉዳዮችን ይዞ ሲሰራበት የነበረ ቢሆንም በሚፈለገው ደረጃ ስራውን ውጤታማ አድርጎ ለመምራት እንዲቻል ይዘት ከነበረው የሚያስጨምር እና የነበሩትን ለአፈጻጸም እንዲያመቹ በማድረግ እንደገና ማስተካከል አስፈላጊ ሆኗል፡፡

በዚህ ረገድ ዋና ዋና የሚከተሉት ጉዳዮች ተጠቃሽ ናቸው፡- ወንጀሎቹን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በአለም አቀፍ ደረጃ የሚደረገውን ትብብር ለማጠናከር ኢ-መደበኛ የትብብር ማእቀፍ እንዲዘረጋለት እና ሕጋዊ እውቅና እንዲያገኝ ማድረጉ ነው፡፡ የፋይናንስ እና ፋይናንስ ነክ ያልሆነ የሙያ እና የንግድ ተቋማት ወንጀሎቹን በመከላከል እና በመቆጣጠር ረገድ ተቋማቸውን እና የሚያመርቷቸው ምርቶች ወደ ገበያ ከመልቀቃቸው በፊት እና በኃላ የስጋት ጥናት እንዲያከነውኑ፣ አመንጪ ወንጀሎችን በግልጽ ማስቀመጥ የሚገባ ሲሆን ከዚህ በፊት የነበረው አቀማመጥ ለአፈጻጸም አስቸጋሪ እና የማያመች እንዲሁም ለትርጉም የተጋለጠ በመሆኑ በዚህ አዋጅ ግልጽ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በተለያየ ቦታ የተቀመጠው የወንጀል ቅጣቶች ከፍተኛ በመሆናቸው አንዳንዱ ቦታ በተለይም የገንዘብ ቅጣት አነስተኛ መሆናቸው አስተማሪያው ቅጣት መስጠት የሚያስችል ይዘት አለመኖሩ፡፡ ተጠቃሚ ባለሀብቶች በአግባቡ መለየት የሚገባቸው በመሆኑ ይህንኑ በግልጽ የሚመለከት ድንጋጌ እስፈላጊ በመሆኑ፣ ሕገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል ድንበር የሚሻገሩ ገንዘቦችን መግለጫ መስጠት ግዴታ እንዲሆን በሀሰት የሚሰጡ መግለጫዎች ወንጀል እንዲሆን ማድረግ ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

## የአዋጁ አወቃቀር

አዋጁ ሰባት ክፍሎች እና በ55 አንቀጾች የተደራጀ ነው፡፡ በክፍል አንድ ጠቅላላ ድንጋጌዎች፣ ክፍል ሁለት የወንጀል ጥፋቶች እና ቅጣት፣ ክፍል ሶስት ወንጀሎቹን ለመከላከል የሚያስችሉ ድንጋጌዎች፣ ክፍል አራት ወንጀሎቹን መቆጣጠር የሚያስችሉ ድንጋጌዎች፣ ክፍል አምስት ወንጀሎችን ለመለየት የሚያስችል ምርመራ፣ ክፍል ስድስት

ዓለም አቀፍ ትብብር የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በስተመጨረሻም በክፍል ሰባት ልዩ ልዩ ድነጋጌዎችን ይዟል፡፡

<u>በአዋጁ የተካተቱ ዋና ዋና ድንጋጌዎች ይዘት</u>

በትርጉም ክፍል ውስጥ በአንቀጽ 2(2) በቀድሞ ከተቀመጠው አዋጅ የአመንጪ ወንጀል ትርጉም አዲስ ትርጉም እንዲይዝ ተደርጓል፡፡ ቀድሞ በነበረው አዋጅ  አመንጪ ወንጀል ትርጉም ሲቀመጥ ማንኛውም ወንጀል ከአንድ ዓመት ቀላል እስራት በላይ የሚያስቀጣ እንደሆነ የተቀመጠበት ነው፡፡ይህ መሆኑ  መነሻ ቅጣታቸው አንድ ዓመት ቀላል እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች የትኞቹ እንደሆኑ መለየት ስለማይቻል አሻሚ ሆነዋል፡፡ቀድሞ የነበረው ትርጉም የወንጀል  ፍሬው አነስተኛ በሆኑ  ጉዳዮችን ጭምር በዚህ ሥርዓት ውስጥ እንዲካተት በማድረጉ ከአምንጪ ወንጀሉ በላይ የሚያስቀጣ ቅጣት ሥርዓት ውስጥ እንዲገባ ያደረገ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት አቃቤ ህግ አዋጁን ጠቅሶ ክስ ከመመስረት ይልቅ የፍታሐዊነት ጥያቄ በማንሳት አመንጪ ወንጀሉን ብቻ በመክሰስ የነበረውን አዋጅ ተፋጻሚ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ ይህም በአጠቃላይ የሕግ አፈጻጸም ላይ ክፍተትን ፈጥሯል፡፡

ይህንን ችግር ለመቅረፍ እና ግልጽ ለማድረግ እንዲሁም የዚህ አዋጅ ዋና አላማ ለማስፈጸም አመንጪ ወንጀልን በድጋሚ መተርጎም አስፈላጊ ሆኗል፡፡  በመሆኑም አመንጪ ወንጀል አሁን ያለውን ትርጉም እንዲይዝ  ተደርጓል፡፡ በትርጉም አሰጣጥ ላይ የተከተለው ስርዓት በአለም አቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያ የፈረመቻቸው ህጎች ላይ የተቀመውን ስርዓት በመከተል ነው፡፡ ይሄውም አመንጪ ወንጀሎችን ዘርዝሮ የማስቀመጥ( Listing approach) እና የመነሻ ገደብ/መጠን በማስቀመጥ(Threshold approach) ነው፡፡ በዚህ መሰረት በትርጉሙ እንዲካተት የተደረገው በወንጀል ድርጊት ውስጥ ያለውን የገንዘብ መጠን እና ወንጀሎችን በዝርዝር በግልጽ በማስቀመጥ ነው፡፡ የገንዘብ መጠኑ ከአምስት መቶ ሺህ ብር  በላይ እንዲጀምር የተደረገ ሰሆን ይህም የሆነበት በአገሪቱ ላይ ጉዳት የሚያስከትል እና የፋይናንስ ስርአቱን ሊያነጋ የሚችል የገንዘብ መጠን ከተጠቀሰው በላይ እንደሆነ ግምት በመውሰድ ነው፡፡  አመንጪ የወንጀሎችን  ዝርዝር ማስቀመጥ( Listing approach) በተመለከተም የአዋጁን ዓላማ ለማስፈጸም ታሳቢ በማድረግ እንዲሁም ሀገሪቷ የፈረመቻቸዉን አለም አቀፍ ስምምነቶች ላይ ሀገራት ህጋቸዉ ዉስጥ  አመንጪ

ወንጀሎች ብለዉ ሊያካትቱ ይገባቸዋል የተባሉ ወንጀሎችን ማካተት ስለሚገባ በዚሁ መሰረት እንዲካተቱ ተደርገዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በአዋጁ አንቀፅ 2(3) ለንብረት ትርጉም የተሰጠው ሲሆን በአሁን ወቅት ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉትን ንብረቶች መካተት ስላለባቸው እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

<u>በወንጀል ተግባር ተግባር የተገኘ ገንዘብን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረግ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ወንጀልን እና ተቀጽላ ወንጀሎችን እንዲሁም በተመለከተ፡፡</u>

በወንጀል ተግባር የተገኘ ገንዘብን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን ወንጀል የሚያደርግ ድንጋጌ በአንቀጽ 3 ላይ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ከቀድሞ አዋጅ ይዘት በተለየ መልክ በዚህ አዋጅ እንዲስተካከል የተደረገው አንደኛ ቅጣትን በተመለከተ ነው፡፡ ቀድሞ የነበረው ቅጣት አመንጪ ወንጀልን የፈጸመ፣ በወንጀል ተግባር የተገኘ ገንዘብን ለመደበቅ እና ለመሰወር ያገዘ ወይም የተባበረ፣ ዋናውንም ወንጀል የፈጸመ፣ የተሳተፈ፣ ያደመ፣ የረዳ፣ እንዲፈጸም ያማከረ እና ያመቻቸ ወዘተ ተግባርን ወይም ድርጊትን የፈጸሙ ሰዎች የተሳትፎ ደረጃቸው ሳይለይ ተመሳሳይ ቅጣት እንዲጣልባቸው የሚያስደርግ ነበር፡፡ ሁለተኛ የገንዘብ መቀጮ ቀድሞ የነበረው አዋጅ በወጣበት ዘመን የሚሰራ ቢሆንም ሀገሪቷ ላይ አሁን ባለው የዋጋ ግሽበት ሳቢያ  የገንዘብ መቀጮ  አነስተኛ በመሆኑ ይህም እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በተቀጽላ ወንጀሎች ሊጣል የሚችለው የገንዘብ አነስተኛ በመሆኑ ይህም እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ ሽብርተኝነትን በገንዘብ መደገፍ የወንጀል ድርጊት የገንዘብ ቅጣትን በሚመለከት በተመሳሳይ እንዲያድግ ተደርጓል፡፡ሌሎች ወንጀሎችን በሚመለከት የገንዘብ ቅጣቱ በማነሱ ምክንያት ከፍ እነዲል ተደርጓል፡፡ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ላይ የገንዘብ ቅጣቱ በማነሱ ተጨማሪ የገንዘብ ቅጣትም እንዲጣልበት የሚያስችል ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

<u>ወንጀሎቹን መከላከል በተመለከተ</u>

በአዋጅ ቁጥር 780/2005 አንቀጽ 3 ላይ ጥሬ ገንዘብና ለአምጭው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን ድንበር አቋርጦ ስለማጓጓዝ በሚል በተደነገገው ውስጥ ኃላፊነት ያለበት ተቋም አሁን ጉምሩክ ኮምሽን በመሆኑ በዚህ አዋጅ 9(1) ላይ እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡ ማንኛውም ሰው ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ወይም ከኢትዮጵያ ሲወጣ የያዛቸውን ገንዘብ፣ ላምጭው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን፣ የከበሩ ድንጋዮች ወይም የከበሩ ብረቶችን ለጉምሩክ

ኮሚሽን "ማሳወቁ እንደተጠበቀ ሆኖ ሲጠየቅም ማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡ ሂደቱም አለም አለም አቀፍ ትብብሮችን በሚያበረታታ እና አለም አቀፍ የንግድ ክፍያ ስርአቶችን እና የካፒታል እንቅስቃሴ በማያሥተጉዋጉል መርህ የሚከናወን እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ በተጨማሪም በአንቀጽ 9 ንዕስ አንቀጽ 3 ላይ የጉምሩክ ኮምሽን ስራውን መስራት እንዲችል ምንጩን እና ለምን አላማ እንደሚውል ተጨማሪ መረጃ የመጠየቅ ስልጣን ተጨምሮለታል፡፡ ይህም በ 7ተኛው የኢሰምላግ(ESMAALG) ግምገማ ውጤት መሰረት እነዚህ ኃሳቦች በአንቀጹ ያለመገኘት እንደ አንድ ጉድለት የተነሳ በመሆኑ እንዲሁም ባለስልጣኑ ከግለሰቦች ተጨማሪ መረጃ በተለይም ስለገንዘብን፣ ለአምጭው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን፣ የከበሩ ድንጋዮች ወይም የከበሩ ብረቶችን ምንጭ እና አላማ ማወቅ ህጋዊ የሆኑ እና ህገ-ወጥ ዝውውሮችን ለመለየት ስለሚረዳ ይህም ወንጀሉን ለመከላከል እንደ አንድ ግብአት የሚጠቅም በመሆኑ ነው፡፡

የቋማት የትብብር ስራንም በተመለከተ በአንቀጽ 9(6) እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ይህም ንኡስ አንቀጽ የተጨመረበት ምክንያት፤ገንዘብን፣ ለአምጭው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን፣ የከበሩ ድንጋዮች ወይም የከበሩ ብረቶችን አስመልክቶ ሀሰተኛ መግለጫ የተሰጠ ጠባቸው በመዛግብት መያዝ እንዳለባቸው ምክረ ኃሳብ 32.8 ስለሚያመላክት ብሎም የሀሰተኛ መግለጫ የተሰጠባቸው ወይም መግለጫ ሳያቀርብ ለማለፍ የተሞከሩ ገንዘብን፣ ለአምጭው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን፣ የከበሩ ድንጋዮች ወይም የከበሩ ብረቶችን የዝውውሮች የአመንጭ ወንጀልን ለመፈጸም ብሎም ለንብረት ማጠብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀልን በተመለከተ የፋይናንስ ኢንተለጀንስ ክትትሎችን ለመስራት መሰረት የሚሆኑ በመሆናቸው ባለስልጣኑ ጥርጣሬ ካለባቸው ዝውውሮች በተጨማሪ የሀሰተኛ መግለጫ የተሰጠባቸው ወይም መግለጫ ሳያቀርብ ለማለፍ የተሞከሩ ሪከርዶችን ለተቋሙ መላክ ወንጀሉን ከመከላከል አንጻር አስፈላጊ እርምጃ እንደሆነ ስለታመነ ነው፡፡ በመሰረቱ ጥሬ ገንዘብና ለአምጭው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን ድንጋዮችን ወይም የከበሩ ብረቶችን ድንበር አቋርጦ በህገወጥ መንገድ የማጓጓዝ ወንጀል እንዲሁም በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል፤ በአመንጭ ወንጀል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል በባህርያቸው ውስብስብ የሆኑ እና ከፈተኛ መጠን ያለው ሃብት የሚያንቀሳቅሱ በመሆናቸው አግባብ ያላቸው ባለስልጣናት ርብርብን ይጠይቃል ፡፡ በተለይም መረጃን ከመለዋወጥ ፤ ወንጀለኞች ከፍትህ ስርአቱ እንዳያመልጡ ከመከላከል አንጻር ከፍተኛ ሚና

ይኖራቸዋል ፤በመሆኑም ይህ ንኡስ አንቀፅ 6 አግባብ ያላቸው ባለስልጣናት ከማስተባበር አንጻር አስፈላጊ በመሆኑ ተጨምሯል ፡፡

## <u>ወንጀሎቹን መቆጣጠር በተመለከተ</u>

የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ሥልጣንና ተግባርን በሚመለከት በአንቀጽ 20 ላይ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡ ይሄውም በአንቀጽ 20(1) ላይ ከዚህ በፊት ይመረምራል የሚለው ቃል ሰፊ ትርጉም ያለው በመሆኑ ከተቋሙ የሥራ ባህሪ አንጻር ያጠናል በሚል እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 20(8) ላይ በተመሳሳዩ የአዋጁ ክፍል በንኡስ 8 ቀድሞ ተካቶ ከነበረው አዋጅ መሰረት የተቀበላቸዉን ሪፖርቶች፣ ለህግ አስፈፃሚ አካላት የተመሩ ጉዳዬችን፣ ከተመሩት ዉስጥ ምርመራ የተካሔደባቸዉንና ክስ የተመሰረተባቸዉ፤ የወንጀል ጉዳዬችን›› ከሚለው ሀረግ በኃላ ‹‹የፍርድ ውሳኔ የተሰጠባቸውን እና ዓለም አቀፍ ድጋፍ የተጠየቀባቸዉና መልስ የተሰጠባቸው ጉዳዬችን ጨምሮ›› የሚል ተካቶበት ስራዉን በተመለከተ የተሟላ ስታትስቲክስ ይይዛል፤በሚል ተስተካክሏል፡፡

በአንቀጽ 20 ንኡስ አንቀጽ (10) ቀድሞ የነበረውን በመከተል የዚህን አዋጅ ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ በራሱ ወይም ከሚመለከታቸዉ ተቆጣጣሪ ባለስልጣናት ጋር በመተባበር የፋይናንስ ተቋማት ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎችና ከሚለው ሀረግ በኋላ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችም ተካተው ቁጥጥር፣ ፍተሻና ክትትል እንደሚያደርጉ የተገለጸ ሲሆን በተጨማሪም ማዕከሉ ግዴታዎቻቸዉን እየተወጡ እንዳልሆኑ ወይም ያልተወጡ መሆናቸዉን ሲደረስበት ይህንኑ ለሚመለከታቸዉ ተቆጣጣሪ አካላት ያሳዉቃል።የሚል ሐረግ ተካቶበታል፡፡

## <u>ምርመራን በተመለከተ</u>

ወንጀሎቹን ለመለየት እና የወንጀል ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የምርመራ ሂደት የሚካሄድባቸው የምርመራ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ እንዲካተቱ ተደርገዋል፡፡ የድንጋጌዎቹ ይዘት ከዚህ ቀደም የነበረው አዋጅ ይዘት የነበረውን በመከተል የተቀመጡ ሲሆን የተወሰኑ ጉዳዮች እንዲስተካከሉ እና እንዲጨመሩ ተደርገዋል፡፡ ከተጨመሩትም መካከል አንደኛዉ አስቸኳይ ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ መርማሪዉ አካል የአቃቤ ሕግ የበላይ ሀላፊ ሲፈቅድ ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ የወንጀል ፍሬን ተከታትሎ ለመለየት በባንክ ሂሳቦች እና በሌሎች

ተመሳሳይ ሂሳቦች ላይ ክትትል ለማድረግ፤ የኮምፒዉተር ሥርዓቶችን፣ መረቦችንና ሰርቨሮችን ለመለየት፣ መገናኛዎችን በክትትል ሥር ለማዋል ወይም ለመጥለፍ፤የደብዳቤ ልዉዉጦችን ለመጥለፍ እና ለመያዝ፤ በሽፋን ሥር ስለሚደረግ ምርመራ( Undercover operation) እና በቁጥጥር ስር የሚደረግ ማስተላለፍን ጨምሮ መርማሪዉ አካል ምርመራ ማድረግ እንደሚችል በአንቀፅ 32(3) ተካቷል፤ ከዚህም በተጨማሪ በቁጥጥር ስር የሚደረግ ማስተላለፍን( Controlled delivery) በአዋጁ አንቀጽ 2(11) ሥር ትርጉም እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡

## ዓለም አቀፍ ትብብርን በተመለከተ

ወንጀሎችን በመከላከል እና በመቆጣጠር ረገድ አለም አቀፍ ትብብር ከፍተኛ አስተዋጾ የሚያበረክት ነው፡፡ ከአንቀጽ 36 ጀምሮ አለም አቀፍ ትብብርን በተመለከተ የተቀመጡ አንቀጾች ተጨማሪ ድንጋጌዎችም የተካተቱበት ሲሆን ለዚህም መሰረት የሆነው ኢትዮጵያ በፋይናንስ ግብረ ሀይል ከተቀመጡት ምክረ ሀሳቦች የነበረብን ክፍተት በሚሞላ መልክ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡ በወንጀል ጉዳዮች ዓለም አቀፍ ትብብር ምክረሃሳብ (FATF) 37, 38 እና 39 ላይ በምክረ ሀሳብ 37 መሰረት ሀገራት በዋናነት በወንጀል ጉዳዮች ዓለም አቀፍ ትብብር የሚጠይቅና የሚቀበል አንድ አካል(Central authority) እንደሚያስፈልግ የተገለፀ ሲሆን ይህም አካል ጥያቄዎቹን ሲቀበልና ሲመልስ ግልፅ የሆነ የጊዜ ገደብ፤ ጥያቄዎቹን ቅድሚያ የሚሰጥበት ስርአት እንዲሁም ኬዝማኔጅመንት ሊኖረው እንደሚገባ ያስቀምጣል፡፡ በመሆኑም እነዚህን ነገሮች የሚያካትት ድንጋጌዎች በአዋጁ እንዲካተቱ ተደርጓል፤

በአዋጅ ቁጥር 943/2010 እንቀፅ መሰረት የፍትህ ሚኒስቴር ስልጣን እና ተግባር ዉስጥ አንዱ በወንጀል ጉዳዮች ዓለም አቀፍ ትብብር ማድረግ በመሆኑ፤ የሚመጡ አለም አቀፍ የህግ ጉዳዮች ትብብር ጥያቄ እና ምላሾች የሚሰጡት በዚሁ ተቋም በመሆኑ በማእከላዊ ባለስልጣን (Central authority) እንደሆኑ በአዋጁ በግልፅ ተመላክቷል፤ ነገር ግን የፋይናንስ ደህንነት አገልገሎትን ጨምሮ ሌሎች መሰል የመንግስት ተቋማት ከአቻ የዉጪ ተቋማት ጋር መደበኛ ያልሆነ ትብብር( Informal cooperation) ማድረግ ይችላሉ፡፡

## ማጠቃለያ

በወንጀል ተግባር የተገኘ ገንዘብን ሕጋዊ አስመስሎ መቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን መከላከል እና መቆጣጠር ትኩረት የሚያስፈልገው ጉዳይ እና አለም አቀፍ ግዴታን ከመወጣት ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

ወንጀሎቹ ከግዜ ወደ ጊዜ ባሕሪያቸው እየተቀያየረ እና እየተወሳሰበ የሚሄዱ በመሆናቸው ሕጎችን፣ አሰራሮችን፣ አለም አቀፍ ልምዶቹን እየፈተሹ ተከታታይ የማሻሻያ ስራዎችን በመስራት መከላከል እና መቆጣጠር ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መሰረት ቀድሞ የነበረውን አዋጅ በጥናነት እና የአገራትን ተሞክሮ እንዲሁም አለም አቀፍ የፋይናንስ ግብረ ኃይል ምክረ ሐሳብን በመከተል ይህ አዋጅ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ በአዋጅ ውሥጥ የተካተቱት ድንጋጌዎች ወንጀሎቹን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር እንዲሁም አለም አቀፍ ግዴታን ለመወጣት የሚያስችሉ ናቸው፡፡